በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር 1-31 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

## እንዲሁም በጃንዋሪ 2024

## የሚኖረው ወርሃዊ የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 1/1/2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ........ - 1 -

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ - 2 -

የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........ - 2 -

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 2 -

ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ - 3 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 3 -

ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከዴሴምበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረውየእርጥበት ሁኔታ ........ - 4 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 4 -

ካርታ 13 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........ - 4 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ ........ - 5 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........ - 5 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........ - 6 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በዲሴምበር በመጀመሪያው እና በሁለተኛዉ አስር ቀናቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ ይሁን እንጂ በሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ደግሞ የዝናቡ መጠንና ስርጭት የመቀነስ አዝማሚያ የታየበት ነበር፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የተስተዋለበት ወር ነበር፡፡


በአጠቃላይ በዲሴምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ የተስተዋለበት ቢሆንም፤ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በአርባ ምንጭ 46.8፣ 3.0፣ 8.6፣ 22.7፣ በብላቴ 15.4፣7.6፣ በጎሬ 28.3፣ 4.2፣ 2.7 እና 0.5፣ በጅማ 3.9፣ 5.4፣ 2.5፣ 1.4 እና 6.6፣ በአማን 7.1፣ 1.6፣ 20.8፣ 2.9፣ 2.2፣ 5.7፣ 6.5፣ 1.4፣ 5.0 እና 10.6፣ በአንገር ት15.3 እና 3.6፣ በአሶሳ 2.1፣ በበደሌ 14.0፣ በቦሬ 7.9፣ 3.2፣ 1.4፣ 8.0፣ 6.6፣ 3.6 እና 12.0፣ በቡሬ 20.5፣ 3.7 እና 5.0፣ በቡርጂ 8.5፣ 33.0፣ 14.6 እና 1.9፣ በጭራ 32.3፣ 6.0፣ 7.7፣ 2.7፣ 1.4፣ 45.2 እና 3.6፤ በፉኚዶ 2.5፣7.7፣ በጋቲራ 5.3፣ በቡሌሆራ 5.5፣ 3.4፣ 1.5 እና 9.3፣ በጂንካ 9.9፣10.7፣ 33.3፣ 10.8 እና 1.6፣ በኮንሶ 5.0፣ 10.8፣ 12.0 እና 4.5፣ በሊሙገነት 4.3፣ በማጂ 8.0፣ 7.0 እና11.5፣ በማሻ 10.6፣14.6፣ 6.0 እና 12.6፣ በምዕራብ አባያ 6.0፣12.0 እና 5.0፣ በሳዉላ 27.2፣ 3.5 እና 5.2፣ በሻምቡ 2.7፣ 15.2፣ 2.5 እና 5.2፣ በኮንሶ 10.8 እና 4.5፣ በቁሉምሳ 11.0፣ በማጀቴ 1.3፤ በፓዌ 11.8፣ በቴፒ 1.4፣ 3.6፣ 1.3፣ 4.7፣ 15.9 እና 1.8፣ በወላይታ ሶዶ 12.8፣ በባሌ ሮቤ 4.7፣ በአሊያ 36.4፣ በአርሲ ሮቤ 2.0፣ በደብረ ወርቅ 1.1፣ በዶሎመና 10.0፣ በእንዋሪ 0.7፣ በጋምቤላ 18.4፣ በጋቲራ 11.8፣ በወሊሶ 0.3፣ በጂንካ 2.2 እና 42.1፣ በሊሙገነት 11.5፣ በሚኤሶ 33.0፣ በቴፒ 1.3፣ 4.7፣ 15.9 እና 1.8፣ በተርጫ 1.5፣ በወላይታ ሶዶ 0.1፣ በያበሎ 2.5 እንዲሁም በየትኖራ 0.3 በሚ.ሜ ይገኙበታል።




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፈው የዲሴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም የደቡብ ኢትዮጵያ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች እንዲሁም የምስራቅ ወለጋ ሰሜናዊው ክፍል ከ31-125 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-12 ቀናት ያህል ያገኙ ሲሆን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ የአሶሳ፣ ካማሺ፣ የማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ እና የመተከል ዞኖች፤ ሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም፣ የምዕራብና የምስራቅ ወለጋ ዞኖች፣ ኢሉባቡር፣ ጅማ፣ ባሌ፤ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ እንዲሁም ቦረና፤ ሁሉም የሲዳማ ዞኖች በተጨማሪም የምዕራብ ሀረርጌ ጥቂት ቦታዎች ላይ ከ3-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 9 እና 10)፡፡

ባለፈው የዲሴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ ክልል የምዕራብ ጎንደር፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሁሉም ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የሲዳማ እንዲሁም የምዕራብ ሀረርጌ ኪስ ቦታዎች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛው በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 11) ።





ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ የሚኖረው የዝናብ መጠን




ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው
የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የዲሴምበር ወር ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታው በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስተዋለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የሰብል ስብሰባቸውን ለሚያካሂዱ አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ በአንፃሩም በመጀመሪያው እና በሁለተኛዉ አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ የእርጥበት ስርጭት የታየበት ሲሆን፤ በሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ግን የእርጥበቱ መጠንና ስርጭት ቀስ በቀስ የመቀነስ አዝማሚያ ነበረው። ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስተዋለው እርጥበታማ ሁኔታ በተለይም የበጋን ወቅት እንደ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ለሚጠቀሙ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና ነበረዉ (ካርታ 12)፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 12 ኢ.ኤ.አ ከዴሴምበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረውየእርጥበት ሁኔታ

## ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ዲሰምበር ወር በጥቂት የላይኛዉ ባሮ አኮቦ፣ የታችኛው ኦሞ ጊቤ እና በጥቀት የስምጥ ሸለቆ ኪስ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ግን ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የአየር ጠባይ አመዝኖባቸው ተስተውሏል (ካርታ 13) ፡፡




ካርታ 13 ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በሚቀጥለው የጃንዋሪ ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማው የአየር ጠባይ ይስተዋልባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ከወሩ አጋማሽ በኋላ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከደመና ሽፋን መጨመር ጋር ተያይዞ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ የጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂና የቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የመካከለኛዉ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 8)፡፡ በተጨማሪም ከአማራ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፤ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች እንዲሁም የሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከኦሮሚያ ክልል የሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ የምስራቅና የምዕራብ ሀረርጌ እንዲሁም ድሬዳዋና ሃረሪ፤ የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች እንዲሁም ከአፋር ክልል ዞን 2፣ 4፣ 3 እና 5 በወሩ የመጀመሪያዎቹ ቀናት ላይ ቀላል መጠን ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ያገኛሉ። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናትም በሰሜን ምስራቅ፤ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚስተዋል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የጃንዋሪ ወር የሚኖረው የአየር ጠባይ በአብዛኛው የመኸር ሰብል ተጠቃሚ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል ከወሩ አጋማሽ በኋላ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በተለይም ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የመካከለኛዉ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ የሚኖረው



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ዘግይተው ለተዘሩ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑትና ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱ የሀገሪቱ አከባቢዎች ለሚያከናውኑት የእንስሳት ልማትም ሆነ፣ ለሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ የእርጥበት ሁኔታው በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ የበልግ እርሻን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲሻሻል የሚረዳ ሲሆን፤ ይህም ለበልግ ወቅት የማሳ ዝግጅት ለማከናወን አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የጃንዋሪ ወር በታችኛው እና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በገናሌ ዳዋ፣ በመካከለኛው አባይ፣ በላይኛው አዋሽ፣ በላይኛው ዋቤ ሸበሌና በመካከለኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ያገኛሉ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et